# የተፈጠነ የወንጀል ፍርድ ሂደት በኢትዮጵያ የፍትህ አስተዳደር ስርአት ላይ ያመጣው ለውጥ

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች:-**

ሰላም አብርሃም

ሰብለ ገ/ጊዮርጊስ

ተወዳጅ እሸቱ

ይልቃል ጌትነት

አዱኛው አንተነህ

ፋሲል ሳሙኤል

1. በተፈጠነ የወንጀል ፍርድ ሂደት አሰራር ጉዳዮችን የሚያዩ አካላት(ዳኞች፤ዐቃቤ ህጎችና ፖሊሶች)አሰራን በተመለከተ ተከታታይ የሆነ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፤

2.የአሰራሩን ውጤታማነት ለማረጋገጥ የህብረተሰቡን ንቁ ተሳትፎ እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ ስለአሰራሩ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኝ ማድረግ ያስፈልጋል፤

3.አሰራሩ ውጤት እንዲኖረው ለማድረግ በአሰራሩ ውስጥ ያሉ የፍትህ አካላት የስራ ድርሻን እና በተፈጠነ የወንጀል ፍርድ ሂደት የሚታዩ የወንጀል አይነቶችን በተመለከተ እንዲሁም ሌሎች ከአሰራሩ ሂደት ጋር በተያያዘ ግልፅ መሆን ያለባቸውን ጉዳዮች የሚያመላክት መመሪያ መዘጋጀት ይኖርበታል፤

4.በፌደራል ደረጃ ይሁን በክልል ደረጃ በተፈጠነ የወንጀል ፍርድ ሂደት አሰራር ውስጥ ያሉ ባለድርሻ አካላት ውጤታማና ወጥ የሆነ አሰራ ይኖራቸው ዘንድ በአሰራሩ ዙሪያ ያላቸውን ተሞክሮ የሚለዋወጡበት እንዲሁም ምክክር የሚያደርጉባቸው መድረኮች መዘጋጀት አለባቸው፤

5.አሰራሩን ተግባራዊ እያደረጉ ያሉት አካላትና ከአሰራሩ ጋር ተያያዥዥነት ያላቸው አካላት(ፍርድ ቤቶች፣ፍትህ ቢሮዎች፣ፖሊስ ጽ/ቤቶች፣ ማረሚያ ቤቶች፣ሆስፒታሎች፣ ወዘተ) በሰው ኃይል እና ለአሰራሩ ውጤታማነት አስተዋፅኦ በሚያደርጉ አቅርቦቶች እንዲጠናከሩ ለማድረግ የአቅም ግንባታ ስራዎች መከናወን አለባቸው

6. የአሰራሩን ውጤታማነት ለማረጋገጥና በየደረጃው የማሻሻያ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችሉ ተከታታይ ግምገማዎችን ማካሄድ ያስፈልጋል፣

7. የተከሳሾችን መብት ለመጠበቅ የሚደረገውን ጥረት ማጠናከር ያስፈልጋል፣በተለይም የህግ ምክክር ከማግኘት ጋር ተያይዞያለውን ችግር ለመቅረፍ ነፃ የህግ አገልግሎቶችንየሚሰጡበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት ይገባል፡፡